ትምህርተ አትናቴዎስ

# ስለ ክርስቶስ የባህርይ አምላክነት

ከኪዳነማርያም ተስፋ

በቅድሚያ ወርኀ ክረምቱን በሰላም አስፈጽሞ፤ ለበጋው ወራትና ለአዲሱ ዓመት፣ለብርሃነ መስቀሉም ላደረሰን አምላክ ምስጋናን በማስቀደም ለመላው ደንበኞቻችን የአክብሮት ሰላምታችንን እናቀርባለን።

ባለፈው ጽሑፋችን ትምህርተ አትናቴዎስ በሚል ርዕስ ቀርቦ የነበረውን ጽሑፍ እንዳጣጣማችሁት ተስፋ በማድረግ በይቀጥላል ያቆየነውን ተከታይ ጽሑፍ ይዘን መቅረባችንን እናበሥራለን። አምላክ አትናቴዎስ ምሥጢሩንና ኃይለቃሉን ይግለጽልን አሜን።

የቅዱስ አትናቴዎስ ትምህርት መሠረቱ ቅዱስ ወንጌል መሆንን እንደሚከተለው ለማረጋገጥ ይቻላል። "ጌታ ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል" ብሎ ጠየቀ እነርሱም አንዳንዶቹ መጥምቁ ዮሐንስ፣ሌሎችም ኤልያስ፣ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት። እርሱም "እናንተስ እኔን ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ" አላቸው ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ "አንተ ክርስ ቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ" አለ ።ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልኽምና ብፁዕ ነህ፤አንተ ጴጥሮስ ነህ፤በዚህችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ በምድር የምታስረው በሰማያት የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል" (ማቴ. ፲፮:፲፫-፳) ይላል።

ቅዱስ ጴጥሮስ ሰውነትን ከመለኮት፣ መለኮትን ከሰውነት አዋሕዶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተገልጦ በዓይኑ የሚመለከተውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አዋሕዶ፤አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ በማለት የእምነት ምስክርነቱን ገልጦአል። ቅዱስ አትናቴዎስም ስለ መድኃኒታችን እንዲህ ይላል "ሰውን ለማዳን ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ሰውም ቢሆን ከአምላክነቱ የጎደለበት የለም። ተለውጦም ሌላ አልሆነም ያው እሱ ነው እንጂ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የነበረ፣ያለ፣የሚኖር ነው እንጂ፤ ሰው ሆኖ በምድር ሳለ ከአብ ዕሪና አልተለየም። ስለዚህ ሰው በመሆኑ ከአምላክነቱ እንዳልተለወጠ፣ አምላክ ስለሆነም በሰውነቱ ሕፀፅ የለበትም።"

ከድንግል ሥጋን ነስቶ ሰው ሆነ ብሎ የማያምን፤ እንደ ነቢያት፣ እንደ ጻድቃን ወይም በቅዱሳን በነቢያት እንደሚያድር አምላክ አደረበት፣አከበረው፣ አጸናው ብሎ የሚያምን፣የሚያስተምር፤ ከተዋሐደ በኋላ ክርስቶስን ከሁለት የሚከፍል እንደምን ክርስቲያን ሊባል ይችላል? በማለት ይጠይቃል። ንግግሩንም በማስረዘም ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ በተመስጦና በአድናቆት እንዲህ ይላል። ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድ ልጅ መሆኑ በዮርዳኖስ ወንዝ፣ በታቦር ተራራ ባባቱ እንደበት የተመሰከረለት እሱን አንዱን፤ ከሁለት ከከፈልነውማ ዕሩቅ ብእሲ ማድረጋችን ነው። የሞተ ውም ለራሱ ብሎ ነው እንደማለት ይቆ ጠርብናል። ዕሩቅ ብእሲ ሰውን ሁሉ ወደሱ ለማቅረብ ችሎታም ሆነ ችሮታ የለውም።መድኃኔዓለም ክርስቶስ ግን፤ የባሕርይ አምላክ እንደ መሆኑ መጠን ሁሉን ወደእርሱ እንደሚያቀርብ ራሱ "እኔ ከምድር ከፍከፍ ያልሁ እንደሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ"(ዮሐ. ፲፪:፴፪) ብሏል።

ነገር ግን ክርስቶስ ፍጡር ነው የሚሉ መናፍቃን፤ በተሳሳተ አስተሳሰባቸው ክርስቲያኖችን መምለክያነ ፍጡር ማለታቸው ድፍረት ነው። ክርስቲያኖች መምለክያነ ፍጡር አይደሉም፤ ዕሩቅ ብእሲን አያመልኩም ብሏል። ከተዋሐደ በኋላ አምላካዊውን ግብር እንደ አምላክነቱ፣ ሰብአዊውን እንደ ሰውነቱ ሠራ የሚሉትን ተጠራጣሪዎች በመቃወም፤ ቅዱስ አትናቴዎስ የእምነት ምስክርነቱን እንዲህ በማለት ይገልጣል። መድኃኒታችን በወንጌል የተናገረው ማንኛውም ቃል፤ በወንጌል የተመዘገበው ድካሙንም፣ ኃይሉንም፣ የገለጠበት ማንኛውም ድርጊት የራሱ የሥጋው ቃል ሥራ ነው። ከኃጢአት በቀር የሰው የሆነውን ሁሉ የራሱ አድርጓልና።

ብዙ ድንቅ ድንቅ ተአምራትን ያደረገው እሱ ተራበ፣ ተጠማ፣ አዘነ፣ አለቀሰ። በጌቴሴማኒ የጸለየው፣ በጎልጎታ መራራ ጩኸት ያሰማው እሱ፤ የእለት ሬሳ ወልደ መበለትን፣ ወለተ ኢያኤሮስን፤ የአራት ቀን ሬሳ አልዓዛርን ያስነሳው ራሱ ሥግው ቃል ነው። ነገረ ምጽአቱን ወይም የራሱን ተመልሶ መምጣት ለደቀመዛሙርቱ ከነገራቸው በኋላ፤ ቀኑንና ሰዓቱን ከመ'ንገር የተቆጠበው ራሱ ሥግው ቃል ነው። አማኑኤል አምላካችን በፅንሰት የጀመረውን የማዳን ሥራ የፈጸመው በሞቱ እንደመሆኑ መጠን። ቅዱስ ጴጥሮስ እንደሰጠው ምስክርነት ያለ ቅዱስ አትናቴዎስም ጽፏል። በሥጋ ርስት፣ በሥጋዌ ሥርዓት እግዚአብሔር ሞተ ብሎ ማመን ክህደት አለመሆኑን ይህ ቅዱስ አባት ይናገራል፡ ነገር ግን ይህንን ልብ ይሏል። አማኑኤል በባሕርዩ መዋቲነት ውላጤ የሚስማማው ነበር ማለት አይምሰለን "ክርስቶስ ተሰቅለ በሥጋሁ በእንቲአነ" ስለዚህ የአማኑኤል መከራ መቀበል በመዋዕለ ሥጋዌ በተደረገው መግቦት ከሆነ፤ እግዚአብሔር ሞተልን ብሎ መናገር ይችላል።

ስለ አማኑኤል ሞት ቅዱስ አትናቴዎስ የሚናገረው ኃይለ ቃል ከቅዱስ ወንጌል ጋር የሚስማማ መሆኑን እናስተውል። አማኑኤል ሞተ ሲባል በፈቃዱ ስለእኛ ሕይወቱን በሞት ለውጦ በሦስተኛው ቀን ተነሣ ማለትን የሚያስረዳ እንጂ፤ ሌላ ጉዳይ አለመሆኑን እንረዳ። "ኢየሱስም መልሶ ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ" አላቸው። ስለዚህ አይሁድ ይህ ቤተመቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፣ አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተመቅደስ ይል ነበር (ዮሐ. ፪:፲፱-፳፩) ይላል።

መዝሙረኛው ዳዊትም አምላክ በሥጋ ሞቶ ሞትን ድል አድርጎ በሦስተኛው ቀን መነሣቱን፣ በአርባኛው ቀንም ደመናትን እየረገጠ ወደ ሰማያት ማረጉን ገልጦአል። "እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፣ የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃያልም ሰው ጠላቶቹንም በኋላቸው መታ" (መዝ. ፸፯(፸፰): ፷፭-፷፮) "አምላክ በእልልታ እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ። ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ፤ ዘምሩ ለንጉሣችን ዘምሩ።" (መዝ. ፵፮(፵፯):፭-፮) ብሏል።

ቅዱስ አትናቴዎስ የተማረው ከመንፈስ ቅዱስ እንደመሆኑ መጠን፤ ትምህርቱ ግልጽና የተብራራ ነበር። የእምነታችንን ምንነት የምንረዳበት በመሆኑ ከዚህ በታች ጽፈነዋል።

፩. "አብ አምላክ ነው፣ ወልድም አምላክ ነው፣ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው። አንድ እንጂ ሦስት አማልክት አይደሉም" ይላል። በዘፍ. ፲፰:፩-፲፭ ያለውንም ስንመለከት ከዚህ ሀሳብ ጋር ይስማማል።

፪. ለአብ ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ አለው፤ ለወልድም ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ አለው፤ ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ አለው።

www.ethiopianorthodox.org

፫. በአካል ሦስት ናቸው ብንልም በመለኮት፣ በባሕርይ፣ በሕልውና፣ በክብር፣ በሥልጣን መበላለጥ አለመኖሩን እናስተውል።

፬. አብ ጌታ ነው፣ ወልድም ጌታ ነው፣ መንፈስ ቅዱስም ጌታ ነው። አንድ ጌታ እንጂ ሦስት ጌቶች አይለደም።

፭. አብ የሚያድን ነው፣ ወልድም የሚያድን ነው፣ መንፈስ ቅዱስም የሚያድን ነው። አንድ እንጂ ሦስት መድኃኒት አይባሉም።

፮. አብ ዘላለማዊ ነው፣ ወልድም ዘላለማዊ ነው፣ መንፈስ ቅዱስም ዘላለማዊ ነው። ዘላለማዊ የሚሆን አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይደሉም።

፯. አብ በማንም አልተፈጠረም አልተወለደም፣ ወልድም ቅድመ ዓለም ከአብ ተወለደ እንጂ አልተፈጠረም፣ መንፈስ ቅዱስ ቅድመ ዓለም ከአብ ሠረጸ። አብ ወልድን መውለዱ በክቡር ዳዊት፣ መንፈስ ቅዱስን ማስረፁ በዮሐንስ ወንጌል ተገልጦአል። "ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል" (ዮሐ. ፲፭:፳፮ ፤መዝ. ፻፱ (፻፲): ፫)

፰. አብ ሁሉን የሚችል ነው፣ ወልድም ሁሉን የሚችል ነው፣ መንፈስ ቅዱስም ሁሉን የሚችል ነው። ሁሉን የሚችል አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይደሉም።

፱. አብ አንድ እንጂ ሦስት አብ አይደለም፣ ወልድም አንድ ወልድ እንጂ ሦስት ወልድ አይደለም፣ መንፈስ ቅዱስም አንድ እንጂ ሦስት መንፈስ ቅዱስ አይደለም።

፲. አብ ወሰን የለውም፣ ወልድም ወሰን የለውም፣ መንፈስ ቅዱስም ወሰን የለውም።

፲፩. ከሦስቱ አካላት አንዱ ከሌላው ቀዳማዊነት ወይም ደኃራዊነት የለውም፤ አንዱም ከሌላው የሚበልጥ ወይም የሚያንስ አይደለም።

ይህ ኃይለቃል እንደሚከተለው ሊብራራ ይችላል። በሰዎች ልማድ አባት ከልጅ እንደሚቀድም የታወቀ ነው። በምሥጢረ ሥላሴ ግን አብ ወልድን ሲወልድ፣ መንፈስ ቅዱስንም ሲያሰርጽ በዘመን አይቀድማቸውም። እንግዲህ እግዚአብሔር በአንድነቱ ሁለትነት፣ በሦስትነቱ አራትነት የሌለበት ነው። ሦስቱ አካላት ግን በባሕርይ በሕልውና በአገዛዝ በሥልጣንና በፈቃድ አንድ ናቸው።

ስለ ሰው ተፈጥሮና በኃጢአት ስለመውደቁ የቅዱስ አትናቴዎስ ትምህርት ከነአርጌንስ አመለካከት የተለየ ነበር። ባለፉት ጽሑፎቻችንን ለመግለጽ እንደሞከርነው ቤተክርስቲያንን ሲያውኪት የነበሩት ቢጽ ሐሳውያን ከፈጣሪ ሳይላኩ ተልከናል፣ ሳይበቁ በቅተናል በማለት በፈቃደ ሥጋና በፈቃደ ሰይጣን በመመራት፣ ውዳሴ ከንቱ አገብሯቸው፤ ትምህርተ ሃይማኖትን ሲያፋልሱ፣ ምሥጢር ሲያጣርሱ እንደነበረ ይታወሳል።

የክህደትና የጥርጥር ትምህርታቸውም በትንፋሽ እንደሚተላለፍ በሽታ ብዙዎችን ጎድቷል። በዚህ ሳቢያ ብዙዎች ከቀና ሃይማኖት ወጥተዋል፣ ከበጎ ምግባርም አድጠዋል። ብርሃን ሲመጣ ጨለማ መድረሻ እንደሚያጣ፤ ከብርሃን ክርስቶስ ብርሃን የጸጋ ትምህርትን የለበሰ ሐዋርያ፤ ክህደት ጨለማን በሚደነቅ ትምህርቱ አስወገደ። ሀሰት ለእውነት ቦታውን ለቀቀ።

ሰው ይላል ቅዱስ አትናቴዎስ "አእምሮ ግዕዛን ያለው ፍጡር ነው ለባዊ ነባቢ ነው የወደደውን ለማድረግ ፍጹም ነፃነት አለው። በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ እንደመሆኑ መጠን አምላኩ የሚወደው አምላኩንም የሚወድ ነው። የመጨረሻ ግቡም ፈጣሪውን መምሰል በምስጋና ከእርሱ ጋር መኖር ነው። ነገር ግን ብርሃን ለብሶና ተጎናጽፎ ከአምላኩ ጋር ሊኖር የተፈጠረው ሰው የፈጣሪውን ትዕዛዝ በጣስ ጊዜ ከክብሩ ወረደ፣ ከማዕረጉ ተዋረደ፣ ከአምላኩ ተጣላ፣ ከጸጋው ተለየ። ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ ያደረገው ጥረት አልተሳካም። ወደ አምላኩም ለመቅረብ አልቻለም። ሞት ጨለማ ስለጠናበት በድንቁርና በቀቢጸ ተስፋ ተዋጠ። በመሥዋዕቱና በጸሎት መዳን አቃተው። እንግዲህ ወደ ቀደመ ክብሩ ይመለስ ዘንድ የፈጣሪው እርዳታ እንደ ሚያስፈልገው አጠያያቂ አይሆንም።"

የቅዱስ አትናቴዎስ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ልብ ይሏል። በዓመተ ፍዳ (ዓመተ ኩነኔ) የሰው ልጆች ሕይወት አስከፊ እንደነበረ በትንቢት መጽሐፍ ኢሳይያስ እንዲህ በማለት ተናግሯል። "ሰማዮችን ቀድደህ ምነው ብትወርድ፣ ተራሮችም ምነው ቢናወጡ፣ እሳት ጭራሮውን እንደሚያቃጥል፣ እሳትም ውኃውን እንደሚያፈላ ስምህም ለጠላቶችህ ይገለጥ።" (ኢሳ. ፲፬:፩-፪) የሰዎች ልጆች ምሕረትን በማያውቅ የጨለማው ገገር፣ በሲያል ጨለማ ተጥለው ይሰቃዩ ስለነበረ፤ በተድላና ደስታ ከሚኖሩበት ገነት ከቸር ፈጣሪያቸው በመጣላቸው የገጠማቸውን የሥጋና የነፍስ ጉዳት የምንመለከትበት ንግግር መሆኑን እንረዳለን።

ጾምና ጸሎታቸው አቅም አንሶት ግዳጅ ለመፈጸም ማለትም ከአምላካቸው ለመታረቅ እንዳላስቻላቸው ውም ነቢዩ ያስታውሳል። "ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፣ ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው፤ ሁላች ንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፣ በደላች ንም እንደ ነፋስ ወስዶናል። ስምህንም የሚጠራ አንተንም ሊይዝ የሚያስብ የለም፤ ፊትህንም ከእኛ ሰውረሃልና በኃጢአታችንም አጥፍተኸናል" (ኢሳ. ፷፬:፮-፯) ይላል።

ቅዱስ አትናቴዎስ እንዲህ ይላል "አዳም ከምድረ ገነት ከመባረሩ በፊት የነበረው ጸጋ ከእምላክ የተሰ ጠው እንጂ የባሕርዩ እንዳልነበረ፤ እፁ ንም ወደ ነበረበት ለመመለስ እግዚአ ብሔር አስፈለገው። ለዚህ አሳዛኝ ፍጡር እግዚአብሔር የመዳኛ ዘዴ ባያገ ኝለትኑሮ በዚህ ባለበት የፍጥረት ሁኔታ ላይ ወደባሰ ጥፋት በደረሰ ነበር። ለሰው ልጅ እንዲያገለግል የተፈጠረ ውም ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ወደነበረ በት ወደ ኢምንት በተመለሰ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ ዝም ብሎ አልተመለከተም። በፊት በረድኤት ሲመግበው ኖረ፤ ኋላም በፍጹም ይቅርታ ለመታረቅ ልጁን ሰደደው፤ በልጁ ሞት ዓለምን አዳነ። "በቀቢጸ ተስፋ የነበረውን የሰው ልጅ ለመታደግ የፍጥረት ባለቤት ወደዚህ ዓለም መጣ። ከንጽሕተ ንጹሐን፣ ከቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያምም ተወለደ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር።"(ኢሳ. ፩:፱) ይላል።

"በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ በሞት ጥላ አገር ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው" (ኢሳ. ፱:፪) ዓለም የዳነው በአምላክ ሰው መሆን ነው። "ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ፣ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል" (ኢሳ. ፱:፮-፯)

"በነጋው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ። አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል፣ ከእኔም በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል ብዬ ስለ እርሱ ያልሁት ይህ ነው። እኔም አላውቀውም ነበር ዳሩ ግን ለእስራኤል ይገለጥ ዘንድ ስለዚህ በውኃ እያጠመቅሁ እኔ መጣሁ። ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መሰከረ መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፣ በእርሱ ላይም ኖረ። እኔም አላውቅም ነበር፣ ዳሩ ግን በውኃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ፤ መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው፣ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ። እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መስክሬአለሁ" (ዮሐ. ፩:፳፱-፴፬) ይላል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።



www.ethiopianorthodox.org